የሰበር መ/ቁ 53064

ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ደሬሳ ኮቱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን - ነ.ፈጅ አልቀረቡም

መዝገቡ በአዳሪ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡

ለአፈፃፀሙ መነሻ በሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ጉዳይ ግራ ቀኙ ተከራክረው በተጠሪ በኩል የተደረገው የሥራ ስንብት ህግ ከደነገገው ውጭ ስለሆነ አመልካች ከልዩ ልዩ ክፍያዎች ጋር ወደ ሥራው ይመለስ ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የተወሰነለትን ውሳኔ ለማስፈፀም የአፈፃፀም ክስ አቅርቧል፡፡ የጠየቀውም ዳኝነት ወደ ሥራ ለመመለስ እንደማይችል ገልፆ በምትኩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(4) መሠረት ካሣ እና የተወሰነለት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ጠይቋል፡፡

አፈፃፀሙን የያዘው የሥር ፍ/ቤትም በአንቀጽ 43(4) መሠረት ለአመልካች እንዲከፈለው የተወሰነ ነገር የለም፡፡ በውሳኔው ከተገለፀው ውጭ ማስፈፀም አይቻልም በማለት ወደ ሥራ መመለሴ ቀርቶ በምትኩ ካሣ ይከፈለኝ የሚለውን ውድቅ አድርጎ ሌሎች ክፍያዎች እንዲፈፀሙለት አዟል፡፡

የአሁን አመልካች የጠየቀው የካሣ ክፍያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን በመግለፅ በየደረጃው በይግባኝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኝነት ቢጠይቅም በተመሳሳይ ምክንያት ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በአሠሪው ችግር ምክንያት ወደ ሥራ ለመመለስ አለመቻሉ ከታወቀ በፋንታው በአዋጅ አንቀጽ 43 መሠረት የካሣ ክፍያ ሊከፈለኝ ሲገባ ይህ መታለፉ የህግ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ሲሆን፤ በዚህ ቅሬታ መነሻ ሁለቱም ወገኖች በሰበር የቃል ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ እኛም ጉዳዩን ተመልክተን እንደሚከተለው ተርጉመናል፡፡

በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በየደረጃው ባሉት ይግባኝ ሰሚውና ሰበር ሰሚው ችሎት የፍርድ ሐተታ ላይ እንደተገለፀው አፈፃፀም የፍርድን ይዘት መሠረት ሊያደርግ ይገባል፡፡ በአፈፃፀም ጉዳይ ከፍርድ ይዘት ውጭ መጨመርም ሆነ መቀነስ እንደማይቻል ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙ ክርክር የመነጨው ከሥራ ግንኙነት ሲሆን የሥራ ግንኙነቱም በአዋጅ ቁጥር 377/96 በሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ ነው፡፡ በዚህም ህግ አንቀጽ 43/3/ ላይ አከራካሪ የሆነው ስንብት ህግ ከደነገገው ውጭ ሆኖ በመገኘቱ ወደ ሥራው እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ወደ ሥራ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ የሥራ ክርክሩን የሚያየው ችሎት መመለሱ ቀርቶ በምትኩ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በማድረግ ሊወሰን እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ ይዘት አንፃር ይኸው መብት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ወደ ሥራ እንዲመለስ ከተፈረደለት በኂላ እንደመሆኑ መጠን ይህ የሠራተኛ አማራጭ የሆነው መብት ተፈፃሚ የሚያደርገው

ችሎት ፍርዱን በማስፈጸም ላይ የሚገኘው ችሎት ስለመሆኑ እንጂ ቀድሞ ፍርዱን የፈረደው ችሎት ሊሆን አይችልም ወደ ሚለው ትርጓሜ ያደርሰናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ሠራተኛው በእራሱ ምርጫም ሆነ በአሠሪው ችግር ምክንያት እንደፍርዱ ወደ ሥራ ለመመለስ ካልፈለገ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ወደ ሥራው እንዲመለስ ፍርድ ማግኘቱ ከተረጋገጠ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) መሠረት በምትክነት በሰጠው መብት መሰረት በመመለሱ ፋንታ ካሣ ሊከፈለው ይገባል፤ ይህንንም የሚያስከፍለው አፈፃፀሙን የያዘው ችሎት ሆኖ እያለ ይህንኑ ድንጋጌ በማለፍ ከተፈረደው ፍርድ ውጭ በመውጣት ማስፈፀም አይቻልም በማለት የአመልካችን የካሣ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአፈፃፀም ክሱን በማመልከት ወደ ሥራ በመመለስ ፋንታ ካሣ እንዲከፈል ውሳኔ አላረፈበትም በሚል ምክንያት የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 17733 በ12/5/2001፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 24165 በ17/11/2001 የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 88091 በ28/3/2002 ዓ.ም የሰጠውን ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሽረናል፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/3/ መሠረት እንደተደነገገው ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ወደ ሥራ አለመመለሱ ከታወቀ በምትኩ ካሣ የማግኘት መብት ያለው ስለሆነ ሊከፈለው ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ሊከፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በአንቀጽ 43/4/ መሠረት አስልቶ ክፍያውን ያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ